***ነሐሴ 20 ቀን 2005 ዓ.ም***

## *በምንሶታ የወያኔ የአባይ ቦንድ ሺያጭ ስብሰባ በሕዝብ ተቃውሞ ከሸፈ*

*ከተለያዩ የሰሜን አሜሪካና የአውሮፓ አገሮች የሚገኙ የወያኔ መንግስት አባላትና በስርዓቱ ተጠቃሚዎች  በሀምሌ ወር ውስጥ  ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ከወያኔ መንግሥት መመሪያና ትእዛዝ በመቀበል ወደ መጡበት አካባቢ ተመልሰዋል። የተሰጣቸውም የቤት ሥራ የአባይን ግድብ ለመገንባት  ቦንድ ሕዝብ እንዲገዛ ቅስቀሳ  ማካሄድ ፣ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በመጥራት የቦንድ ሺያጭ ማካሄድና ገንዘብ መሰብሰብ ፣ ሕዝብ ኮንዶሚኒየም ቤት እንዲገዛ ሁኔታዎችን መመቻቸት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ። ይህን እንግዲህ ከዚህ በፊት ከ2008ዓ.ም ጀምሮ የቤተክርስቲያንና የማህበረሰብ ቦታዎችን መቆጣጠር ፤ ካልተቻለ ማፍረስ ፣ መከፋፈል፣ ግለሰቦችን የቤት መስሪያ ቦታ ይሰጣል በማለት መደለል፣ የተለያዩ ኢንቬስትመንት ሥራዎችን ማካሄድ ለሚፈልጉት  ሁሉ በሮች ሁሉ ክፍት ናቸው በማለት አገር ቤት እንዲገቡ ማድረግና የወያኔ ደጋፊ ማድረግ፣ በገንዘብ ሊያሳስቱ  ለሚችሉት ከ$50, 000,000 መድቦ ማታለልና የወያኔ ደጋፊ ማድረግ ፣ በዘርና በጎሳ ሕዝቡን እንዲከፋፈል ለማድረግ ወያኔ 51 ገጾች ያሉትን መመሪያ በትኖ ተግባራዊ እያዳረጉ ካሉት እንቅስቃሴዎች በተጫማሪ መሆኑ ነው። ዋና ትኩረቱም በውጭ የሚገኘውን ሕዝብ ከተቃዋሚዎች ጎን እንዳይቆም ማድረግ፣ አገር ቤት በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ችግር አይተው እንዳላዩ እንዲሆኑ አፍ መለጎምና  ወያኔን እንዳይቃወሙ ማድረግ ነው። ከምንሶታ ወደ አዲስ አበባ የሄዱት  የወያኔ ደጋፊዎችና ተባባሪዎቻቸው  "የአባይ ቦንድ ቀን በምንሶታ"("Nile Day in Minnesota") በሚል ርዕስ የቦንድ ሺያጭ  በላኦስ ማሕበረሰብ ስብሰባ አዳራሽ ( Laos Community Meeting Hall)  እሑድ ነሐሴ 18 ቀን 2005 (Sunday , August 25, 2013) ከሰዓት በኋላ ከ8 ሰዓት - ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ (2:00pm – 8 :00pm) ሕዝባዊ ስብሰባ እንደሚኖር የሚገልጹ ፖስተሮችን በየንግድ ቤቶችና በተለያዩ ቦታዎች ለጠፉ። የስብሰባው ጣሪዎችም " የሚኒሶታና የአካባቢው ኢትዮጵያውያንና  ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራ ማህበር" ("The Ethiopian Diaspora Association in Minnesota" ) ነን አሉ ። ይኸም ወያኔ  በውጭ ያደራጀው የእንቬስተሮችና የሆዳሞች ጥርቃም መሆኑ ስለሚታወቅ ሕዝቡ ተደፈርን አለ።*

*ሕዝቡ ቁጣውን መግለጽ ጀመረ። ፖስተሮችንም ከተለጠፉበት ካንዳንድ ቦታዎች ማንሳት ተጀመረ። አንዳንድ የዋሕ ኢትዮጵያውያን ባለሱቆችን ከፖስተሩ ጀርባ ያለውን የወያኔን ተንኮል እንዲያውቁ ለማድረግ ጥረቶች ተደረጉ። ሕዝቡም አውነቱን መረዳት ቻለ ። ረቡእ ነሐሴ 21 ቀን 2013 እ.ኢ.አ ከምሽቱ 9 :00- 11:00ፒም በምንሶታ የሚገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በስልክ ኮንፍረንስ (Teleconference) በማካሄድ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት በማካሄድ ስብሰስባው እንዳይካሄድ ለማድረግ እቅድ ወጥቶ በቀረው አጭር ቀናት ውስጥ ህዝቡን ለማንቀሳቀስ ተግባራዊ ስራዎች እንዲሰሩ ተወሰነ። የስብሰባው አዘጋጅ የወያኔ ተላላኪዎችም ውሳኔውን ሰሙት መሰል ከቀኑ 8 ሰዓት ለመጀመር አቅደውት የነበረውን ስብሰባ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ለመጀመር ማሳባቸው ተሰማ። የሕዝብ ጎራም በስልክ መረጃዎችን በመለዋወጥ የወያኔን ሴራ ለማክሸፍ ሰብሰባው ወደ ሚካሄድበት ቦታ ቀድሞ ደረሰ ። ስድስት ሰዓት ላይ ኢትዮጵያውያን የሰብሰባው አዳራሽ የሚገኝበትን ሕንፃ በር ተቆጣጥረው ወያኔዎችንና ተላላኪዎቻቸውን መምጠት መጣበቅ ጀመሩ። እነሱም መጡ ። ሕዝቡን አልፈው ወደ በሩ ለመጠጋት የሞከሩትን  ወያኔዎችና ተላላኪዎች የሕዝቡ ወላፈን ገረፋቸው ። ግርግር ተጀመረ። ፖሊስ ተጠራ። የሕዝቡ ንዴት እየጨመረ ሄደ። መፈክር ተዥጎደጎደ፡-*

- *ወያኔ ሌባ፣ ወያኔ ሌባ ፤ ወያኔ ሌባ ፤ ኢቲቪ ሌባ፣*
- *ከአባይ ግድብ በፊት ግድያ ይቁም!*
- *ከአባይ ግድብ  በፊት የሰው መብት ይከበር !*

- *ከአባይ  ግድብ በፊት የታሰሩት የሙስሊም መሪዎች ይፈቱ !*

- *ከአባይ  ግድብ በፊት የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ !*

- *ከአባይ  ግድብ በፊት ዘረኝነት ይገደብ ! ---ወዘተ የሚሉ መፈክሮችን  ሕዝቡ ማሰማት ጀመረ*

*ከዚያም አካባቢውን በግምት ከ20-25 የፖሊስ መኪናዎች የመጣ የፖሊስ ኃይል ተቆጣጠረ። የተወሰኑ ሰዎችን ከሁለቱም በኩል አሳረ። ስብሰባው ሊካሄድ  እንደማይችል ፖሊስ ገለጸ። የስብሰባ ጣሪዎችና ተቃዋሚዎች ስፍራውን ለቀው እንዲሄዱ ትእዛዝ ሰጠ። ፖሊስ ያሳረቸውን ሰዎች ለቀቀ። ሰውም ወደቤቱ በሰላም ተበትኗል። ለወደፊቱም የወያኔን ሴራ ነቅቶ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ተነጋግሯል። ወያኔ በምንሶታ ሕዝብ ላይ ለማሳየት የሞከረው ድፍረት በውርደት ቅሌቱን እንዲከናናብ አድርጎታል። ሕዝብን ለማያከብር የሚገባው ነው ። ሕዝብ በአሻናፊነት ተወጥቷል። ምንም ጊዜም ሕዝብ ያሻንፋል። የአምባገነኖችና የተባባሪዎቻቸው መጨረሻው ወርደት ነው።*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ*

*ሪፖርት አቅራቢ ፡*

*ሙሉጌታ  ዘሪሁን*